የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)
Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)
www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com

# በወገኖቻችን ላይ የሚካሄደው አፈናና ጭፍጨፋ ባስቸኳይ ይቁም

ታህሳስ 02፣ 2008 (ዲሰምበር 12, 2015)

በአለፉት ሳምንታት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በተለይም በመሀል፣ በምእራብ፣ ምስራቅና ደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ የስርአቱን ፖሊሲዎች በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ ያደረጉ ተማሪወች በገዥው ወያኔ ኢህአዴግ ጸጥታ ሀይሎች መደብደባቸው፣ መታሰራቸውና በጭካኔ መገደላቸው በተለያዩ የዜና ማሰራጫዎች በመገለጥ ላይ ነው።

ወያኔ ኢህአዴግ ላለፉት 24 አመታት እንዳደረገው ሁሉ አሁንም ሰላማዊ ተቃውሞን በሀይል ለማፈን መሞከሩ በሀገራችን ውስጥ አላስፈላጊ የሆነ መካረርን ከማስከተሉም በላይ የሀገራችንን ውስብስብ ችግሮች እጅግ ወደተወሳሰበ ደረጃ ያደርሰዋል።

የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ በገዥው ቡድን ህይወታቸውን ላጡ ወገኖቻችን፣ ለቤተሰቦቻቸውና ለዘመድ አዝማድ እንዲሁም ጉዳት ለደረሰባቸው ሁሉ የተሰማውን ሀዘን እየገለጠ በሰላማዊ መንገድ መብታቸውን ለማስከበር ሁሉም ኢትዮጵያውያን የሚያካሂዱትን ትግል በጉልበት ለማፈን የሚደረገውን ሙከራ ሁሉ በጥብቅ ያወግዛል።

የሀገራችን ዘርፈብዙ ችግሮች በትእግስት፣ በመደማመጥ፣ ባርቆ አሳቢነትና ለህግ በመገዛት እንጂ በጉልበትና ባፈና ሊፈታ እንደማይችል ገዥው ቡድን ሊገነዘብ ይገባዋል። ትላንት ከትላንት ወዲያ እንደተደረገው ሁሉ ዛሬም የዜጎችን ደም በማፍሰስ በማሰርና በማሰፈራራት ተቃውሞን አፍኖ የስልጣን እድሜን ለማራዘም መሞከር እጅግ ሀላፊነት የጎደለው ብቻ ሳይሆን፣ ፈጽሞ ማስተዋል አለመቻልም ነው። ገዥው ቡድን በህዝብ ላይ የሚያካሂደው አፈና ሁሉ እንዳልሰራ በተገነዘበ ቁጥር እጅግ ዘግናኝ ወደሆነ ተጨማሪ ተግባር እየመራ ይገኛል። አሁን ያለው ሁኔታ ወገኖቻችንን በገዥው ቡድን የጸጥታ ሀይሎች እጅግ አሰቃቂ ጭፍጨፋ ሊጠብቃቸው እንደሚችል ያመላክታል።

በድጋሚ የስርአቱ መሪዎች ከዚህ የወንጀል ተግባር እንዲታቀቡ ፣ በህዝብ ላይ ለደረሰው ጭፍጨፋና ስቃይ ተጠያቂ የሆኑ ሁሉ ለፍርድ እንዲቀርቡ እያሳሰብን ሁሉም ኢትዮጵያዊያን አንዱ ዜጋ ሲነካ ሁሉም እንደተነካ በመገንዘብ የስርአቱን የግፍ እርምጃ በጋራ እንዲያወግዙና በጋራ እንዲቋቋሙ ከማንኛውም ጎራ ለሚመጣ የከፋፋይ ሴራ ሰለባ እንደይሆኑ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

የተቃወሚ ድርጅቶችም ሆኑ የሲቪክ ማህበራትም ታራ የፖለቲካ ጥቅም ለማግኘት ከመሯሯጥ ይልቅ ሀገራችንና ህዝባችን ያሉበትን እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ተገንዝበው የህዝባችንን አንድነት አጠናክሮ የሀገራችንን ደህንነት አደጋ ላይ ሳንጥል የስርአት ለውጥ ለማምጣት የህዝባችንን ትግል ማቀነባበር የሚቻልበትን መንገድ ባስቸኳይ ለመፈለግ በጋራ እንድንነሳ የትብብር ጥሪያችንን በድጋሚ እናቀርባለን።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!

Tel: 44 7937600756 , +1 9168486790 E-mail : shengo.derbiaber@gmail.com